DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ይህ በተማሪዎች እና በአጠቃላይ ሕዝቡ፣ ፋይል የተደረጉ ቅሬታዎች ላይ ምላሽ መስጠት ፖሊሲ፣ ከዚህ ቀደም በዚህ-ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና/ወይም መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

**ቻንስለሩ ያጸደቀት:** ____________________

**በስራ ላይ የዋለበት ቀን:** ኦክቶበር (October) 1 ቀን 2021

# በተማሪዎች እና በአጠቃላይ ሕዝቡ፣ ፋይል የተደረጉ ቅሬታዎች ላይ ምላሽ መስጠት

## I. ዓላማ እና የስፋት-መጠን

ሁሉም ተማሪ የመወደድ ስሜት እንዲሰማው፣ እና በአዎንታዊነት ተጽዕኖ የሚያደርግን ማህበረሰብን ለማዘጋጀት እና ጠንካራና ሁሉን አካታች የሆነ የመማሪያ አካባቢዎችን ለሁሉም ተማሪዎች በመስጠት በሕይወታቸው እንዲበለጽጉ መደረጉን ለማረጋገጥ፤ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) በቁርጠኝነት ይሰራል። ይህን ቃል-በመግባት ቁርጠኝነትን ለማሟላት፤ DCPS፣ በተለይ ደግሞ ቀለም ላላቸው ተማሪዎች (students of color) - የዕድሎችን ክፍተት የሚፈጥሩ ነገሮችን በማጥፋት፣ የተቋማትን የተዛባ አመለካከትን ለማስቆም፣ እና ለቀለም-ትምህርት እና ለማህበራዊ ስኬቶች እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች የሚያስወግድ አካባቢን በመፍጠር ላይ ትኩረት ያደርጋል። ከአድልዎ ነፃ የሆነ - እኩልነት ያለው አካባቢን ለማቀርብ፤ በተለይ የበለጠ የመለያየት ልዩነቶች በሚታዩባቸው ነገሮች ላይ DCPS የበለጠ እርዳታዎችን ይሠጣል።

ተንከባካቢ የሆነ፣ ሁሉን-በእኩል አካታች (inclusive)፣ እና አረጋጋጭ የሆነ-አካባቢን ለሁሉም ተማሪዎች የመስጠት - የDCPSን ዓላማ ከፍ-አድርጎ በመደገፍ፤ ሁሉን-አቀፍ አማራጭ መፍትሄ ሰጪ እና ፍትሃዊ-እኩልነት (Comprehensive Alternative Resolution and Equity (CARE) ቡድኑ፣ በDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኛ፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer)፣ እና የኮንትራት ሠራተኛ ወይም ተማሪ የደረሰን - ተገቢ-ያልሆኑ እና/ወይም አድሎአዊ የሆነ አቀራረብን፣ ሪፖርት የማድረጊያ ሜካኒዝምን ያቀርባል።

ይህ ፖሊሲ የሚያስተላልፈው፤ ከቅሬታ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ክሶችን እንዴት - ተገቢ-ያልሆኑ እና/ወይም አድሎአዊ የሆነ አቀራረብን፤ የተማሪዎችን መብቶች፣ ወይም ማንኛውም እያንዳንዱን ተማሪ፣ እንዳያገኙ የተከለከሉት ወይም በአጭር-እንዲቋረጥ የተደረጉ በተደረጉ ሁኔታዎች ውስጥ በሚሆኑ ጊዜ፤ ወይም ማንኛውም ተማሪ ወይም የተማሪዎች ቡድን - በዘፈቀደ ወይም ተገቢ-ባልሆነ ድንጋጌ፣ ሂደት፣ ወይም የፀባይ መደበኛነት ውስጥ ተጠቂ-የሚሆኑበትን ሁኔታ፣ ይህ ሁኔታ በሚከሰት ጊዜ እና በዚህ ሁኔታ ውስጥ DCPS ምላሽ የሚሰጥበት ነው። ይህ ፖሊሲ፣ ለሁሉም የDCPS ተማሪዎች እና ለአጠቃላይ ሕዝቡ[1] በስራ-ላይ ይውላል።

ይህ ፖሊሲ፣ ከዚህ ቀደም በዚህ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

## II. ሥልጣን እና በስራ ላይ የሚውል ሕግ[2]

| ምንጭ | ጥቅስ (Citation) |
|---|---|
| የፌደራል ሕግ | - አንቀጽ 9 (Title IX) የ1972 የትምህርት ማስተካከያ-የተደረገበት ድንጋጌ (Education Amendments Act)፣ (Title IX), 20 U.S.C. § 1681<br>- የ1973፣ ክፍል 504 መልሶ-ማቋቋም ድንጋጌ (Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973)፣ 29 U.S.C. § 701 *et seq.*<br>- አንቀጽ 6 (Title VI)፣ የ1964 የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (Civil Rights Act)፣ 42 U.S.C. § 2000d *et seq.*<br>- የአንቀጽ 2 (Title II)፣ የ1990 የአሜሪካውያን የጉዳተኝነት ድንጋጌ (Americans with Disabilities Act)፣ 42 U.S.C. § 12101 *et seq.* |

[1] Labor Management and Employee Relations investigates complaints involving staff. The Office of Integrity (OOI) also address complaints filed involving staff. For more information contact dcps.lmer@k12.dc.gov or dcps.cio@k12.dc.gov. An online referral form may be submitted to OOI at https://dcps.dc.gov/page/office-integrity-online-referral-form.

[2] Nothing in this policy will supersede federal, state, or local law.

| | |
|---|---|
| የፌደራል ደንቦች | - አንቀጽ 9 (Title IX) የማስፈጸሚያ ደንቦች (implementing regulations)፣ 34 C.F.R. Part 106 |
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት ሕግ | - የ1977 የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (DC Human Rights Act)፣ D.C. Code § 2-1401 *et seq.*<br>- የ2018፣ የትምህርት ቤት የደህንነት-ጥበቃ ኦምኒባስ (Omnibus) ማስተካከያ ድንጋጌ (School Safety Omnibus Amendment Act)፣ D.C. Code § 38-951 *et seq.* and D.C. Code § 38-952 *et seq.* |
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች | - የተማሪ ቅሬታ ሂደቶች (Student Grievance Procedures)፣ 5-B DCMR § 2405<br>- ለወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ እና ጎብኚ-እንግዶች፤ ቅሬታ ሂደቶች (Grievance Procedures for Parents, Guardians, and Visitors)፣ 5-E DCMR § 405<br>- የተማሪ የመብቶች ህግ (Bill of Rights)፣ 5-E DCMR § 2401 |

## III. ቁልፍ-የሆኑ አባባሎች እና ትርጉሞቻቸው

**የተበሳጨ (Aggrieved)** ማለት፤ አንድ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች-ያሉበት ቡድን፤ ተገቢ-ያልሆነ እንክብካቤን የማግኘት ተሞክሮ የገጠማቸው ማለት ነው። የተበሳጨው (aggrieved) እና ሪፖርት የሚያደርገው፣ አንድ-ሰው ሊሆን ይችላል።

**ክስ (Allegation)** ማለት፤ አንድ-ሰው ትክክል-ያልሆነ ነገርን እንዳደረገ - የመብት-ጥያቄን ማቅረብ ማለት ነው።

**የይግባኝ ግምገማ ፓነል (Appeal review panel)** ማለት፤ አቤቱታዎችን እንዲገመግሙ እና በቅሬታዎች ላይ የመጨረሻ የኤጀንሲ ውሳኔዎችን እንዲያደርጉ፣ በቻንስለሩ የተወከሉ ሰዎች ማለት ነው።

**ማንጓጠጥ (Bullying)** ማንኛውም ስር-የሰደደ፣ የተስፋፋ ወይም የተደጋገመ ክንውን ወይም ባህሪይ፤ በአካላዊም ሆነ በኤሌክትሮኒክ ወይም በቃል (verbal) የተደረገ እና በተገቢው ሁኔታ የሚከተሉትን ሊያስከትል ይችላል ተብሎ የተገመተውን ያካተተ ማለት ነው:

- ተማሪውን ይሆናል-ተብሎ በሚገመት አስፈሪ የሆነ የአካላዊ ጉዳት በራሳቸው ላይ ወይም በንብረታቸው ማድረስ፣
- በተማሪው አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ጤንነት ላይ፣ ጉልህ የሆነ የጉዳት-ውጤት የሚያደርስ ነገር መፍጠር፣
- በተማሪው የቀለም-ትምህርት ክንውን ላይ ወይም በትምህርት-ገበታ መገኘት (attendance) ላይ ጉልህ-በሆነ ሁኔታ መስተጓጎልን መፍጠር፣ ወይም
- በተማሪው የመሳተፍ አቅሙ ላይ ወይም ከትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ወይም አገልግሎቶች የሚያገኘውን ጥቅማ-ጥቅሞች ላይ ጉልህ-የሆነ መስተጓጎልን መፍጠር፤ (*see* D.C. Code § 2-1535.01)

**የሰው-ልጅ መብቶች ቅሬታ (Civil rights grievance)** ማለት፤ የአንቀጽ 2 (Title II)፣ አንቀጽ 6 (Title VI)፣ አንቀጽ 9 (Title IX)፣ የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ፣ ወይም በ*ፀረ-መድልዎ ፖሊሲ* ተደንግጎ-የሚገኝ ማንኛውም መብት፤ ተከትሎ ማንኛውም ሪፖርት የተደረገ ወይም አቤቱታ የቀረበበት የጥሰት ክስ: *ተማሪዎች*[3] እና በተማሪ-በተማሪ ላይ የሚፈጥረውን ፆታዊ የሆነ መጥፎ-ባህሪይን መከላከል እና መፍትሄ-መስጠት።[4]

**በሳይበር ሟንጓጠጥ (Cyberbullying)** ማለት፤ ቴክኖሎጂን ወይም የኤሌክትሮኒክ ዲቫይሶችን አማካኝነት - እንደ ስልኮችን፣ የሞባይል ስልኮች (cell phones)፣ ኮምፒውተሮች፣ እና ኢንተርኔትን በመጠቀም ማንጓጠጥ (bullying) ማለት ነው። ይህም የሚያካትተው፤ ነገር-ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ ኢሜል፣ በቀጥታ መልዕክቶችን በመላክ፣ የቴክስት (Text) መልዕክቶች፣ እና በኢንተርኔት ላይ የተለጠፉ-ነገሮች (postings) ናቸው።

**አድልዎ (Discrimination)** ማለት፤ ኢ-ፍትሃዊ ወይም ጭፍን-ጥላቻ ያለው አቀራረብ ለተለያዩ ምድቦች ያሏቸው ሰዎች ማድረግ ማለት ነው። አድልዎ (Discrimination) በርካታ ቅርጾችን የያዘ ሊሆን ይችላል፤ ይህም ስድብ-የያዘ ቀልዶች፣ በመጥፎ ስም-መጥራት፣ ማስፈራሪያዎች፣ ማንጓጠጥ፣ የሳይበርማንጓጠጥ (cyberbullying)፣ ወይም የወሲብ/የአካላዊ ጥቃት በአስተማሪዎች ወይም በተማሪዎች መፈጠርን ያካተተ ነው። ይህን አካትቶ የያዘውም፤ ቃላትን-ያልጨመረ የባህሪይ አገላለጽ፤ እንደ በምስል ወይም በጽሁፍ-ዓረፍተነገሮች ወይም አካላዊ ማስፈራራትን፣ ጉዳት-ማድረስን ወይም ማዋረድን የሚያሳዩ ባህሪያቶችን ነው። (*see* D.C. Code 2-1401, e*t seq.*)

**አጠቃላይ ቅሬታ (General grievance)** ማለት፣ ትክክለኛ-አግባብ የሌለው እንክብካቤ በመደረጉ የተደረጉ ክሶችን ሪፖርት ለማድረግ፤ ፋይል የተደረገ አቤቱታ ሲሆን፤ በተማሪዎች መብቶች ላይ የሚያስከቱ ነገሮችን፣ ወይም ማንኛውም እያንዳንዱ ተማሪ፣ የመከልከል ወይም በአጭሩ-የመቅጨት መንገድን ከተሰጠው፤ ወይም

---

[3] *See Anti-Discrimination Policy: Students*, available at https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.

[4] *See Preventing and Addressing Student-on-Student Sexual Misconduct* Policy, available at https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.

ማንኛውም ተማሪ ወይም የተማሪዎች ቡድን - በዘፈቀደ ወይም ተገቢ-ባልሆነ ድንጋጌ፣ ሂደት፣ ወይም የፀባይ መደበኛነትን አላግባብ እንክብካቤን በሚሰጥ ሁኔታ ተጠቂ በሚሆኑ ጊዜ።

**ቅሬታ (Grievance)** ማለት፤ በትክክለኛ መንገድ እንክብካቤ ያለመደረጉን ሪፖርት ለማድረግ፣ አቤቱታን ፋይል ማድረግ ማለት ነው። ቅሬታዎች (Grievances)፣ በሰው-ልጅ መብቶች ወይም በአጠቃላይ-ምድብ፣ ስር ሊገባ ይችል ይሆናል።

**በቅሬታ ላይ እርዳታ የሚሰጥ ሰው (Grievance Point of Contact (POC)** ማለት፤ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኝ ሰው፤ ቅሬታዎችን ለመቀበል፣ ቅሬታዎችን በተገቢው-ሁኔታ ሪፖርት መደረጋቸውን የሚያረጋግጥ፣ የምርመራውን ሂደት የሚረዳ፣ እና ስለ ቅሬታ ፖሊሲ ለትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስተዋውቅ-ሰው ማለት ነው።

**ቅሬታ አሰሚ (Grievant)** ማለት፤ ቅሬታውን ፋይል የሚያደርገው ሰው ማለት ነው።

**ትንኮሳ (Harassment)** ማለት፤ ያልተጋበዘ ወይም ተቀባይነት-የሌለው ፀባይ ማለት ነው።

**የመፍትሄ ደብዳቤ (Letter of resolution)** ማለት፤ በምርመራው ውጤቶች ላይ ለተዘረዘሩት አካላቶች (parties)፣ የጉዳዩን መዘጋት ሪፖርት የተሰጠበት ማለት ነው።

**አካላቶች (Parties)** ማለት፤ በጉዳዩ ላይ የተበሳጨው እና ምላሽ-የሚሰጠው ሰው ማለት ነው። ሪፖርት አድራጊው፣ የጉዳዩ አካል (party) የሚሆንበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል።

**ቅድመ-ምርመራ (Preliminary investigation)** ማለት፤ ምርመራው ሙሉ ዋስትና የሚሰጥ ክሶች እንዳሉት ለመወሰን፣ ቅሬታው ላይ በቅድሚያ ምልከታ የሚያደርግ ማለት ነው።

**የማስረጃ መደበኛነት ቅድመ-ሁኔታ (Preponderance of evidence standard)** ማለት፤ የቀረበው ውንጀላዎች እውነተኛነት ወይም እውነተኛነት-የሌላቸው መሆኑን-አለመሆኑን መወሰን ማለት ነው። መደበኛ-የሆነውን ያሟላ ነው ብሎ-ለመደምደም እንዲያስችል፤ ከ50% በላይ የሆነው-ማስረጃ፤ ውንጀላዎቹ እውነተኛ እንደሆኑ መጠቆም መቻል አለበት።

**ሪፖርት አድራጊ (Reporter)** ማለት፤ ማንኛውም ግለሰብ፤ የሚከተሉትን ጨምሮ፣ ነገር ግን በነዚህ ብቻ ሳይወሰኑ፤ እንደ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ተማሪ፣ ወይም የትምህርት ቤት ኀብኂ-እንግዳ - ስለተከሰተው ነገር የሚያውቅ እና ቅሬታውን ፋይል የሚያደርግ ማለት ነው።

**ምላሽ-ሰጪ (Respondent)** ማለት፤ አግባብ በሌለው ባህሪይ ተጠያቂ የሆነው - ሰው ወይም ሰዎች፣ ማለት ነው።

**የበቀል-እርምጃ (Retaliation)** ማለት፤ አንድ ሰው ሪፖርት ባደረገው ነገር ምክንያት፣ በአድልዎ ሁኔታዎች ምርመራ ውስጥ በመካፈል ወይም የአድልዎ እንቅስቃሴን በመቃወሙ (ለምሳሌ፤ አቤቱታዎችን በመፈረም) ቅሬታውን ፋይል ስላደረገ፣ ማንኛውም ከፍተኛ የሆነ እርምጃዎች ከተወሰደበት ማለት ነው።

**ደጋፊ የሆኑ እርምጃዎች (Supportive measures)** ማለት፤ ተማሪውን በመወከል - ከቅሬታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎች ናቸው፤ (ለምሳሌ፤ የደህንነት-ጥበቃ ዕቅድን መፍጠር፣ የክፍል-ውስጥ የጊዜ-ሰሌዳን ማስተካከል፣ ማማከር)።

**ሠራተኛ (Staff)** ማለት፤ የትምህርት ቤት ተቀጣሪ-ሠራተኛ ወይም የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer)፣ ትምህርት ቤቱ በኮንትራት የሚሰራበት አካል ተቀጣሪ-ሠራተኛ፣ ወይም ትምህርት ቤቱ እንደ ወኪል ሆኖ ከትምህርት ቤቱ ጋር በትምህርት ቤቱ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚሰሩ፤ ከትምህርት-ቤቱ ጋር በአጋርነት የሚሰራ-አካል ተቀጣሪ-ሠራተኛ ወይም የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛ (volunteer) ማለት ናቸው። (D.C. Code § 38-951.01(5))

## IV. መስፈርቶች

እያንዳንዱ የDCPS ተማሪ፤ መብቶች አሉት[5] - ይህም፣ ከተከለከሉ-ባህሪያቶች የመጠበቅ መብቶችን-ያካተተ ነው። እነዚህ የቅሬታ ሂደቶች የተቀረጹት፣ በDCPS የሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በDCPS-ስፖንሰር የተደረገ እንቅስቃሴ[6] ውስጥ በሚካፈሉ ጊዜ፤ የተማሪዎችን እና የሦስተኛ አካሎችን መብቶች ለመጠበቅ ነው።

ቅሬታዎች፤ አላግባብ የሆኑ እንክብካቤዎችን ሪፖርት አድርጎ ለማቅረብ የሚጠቅሙ ሲሆን፤ ይህም የሚያካትተው፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ ያደርሳል ተብሎ በተጠረጠረባቸው ሁኔታዎች:

- ተማሪው ወይም የተማሪዎች ቡድን፤ አጥጋቢ የሆነ ትምህርታዊ ዕድሎችን ከማግኘት መከልከል፣
- የተማሪው ወይም የተማሪዎች ቡድን መብቶች ሲከለከል ወይም በአጭር-ሲቀጭ፣
- ተማሪ ወይም የተማሪዎች ቡድን - በዘፈቀደ ወይም ተገቢ-ባልሆነ ድንጋጌ፣ ሂደት፣ ወይም የፀባይ መደበኛነት ውስጥ አላግባብ ተጠቂ ሲሆኑ፣
- ተማሪው ወይም የተማሪዎች ቡድን፤ በማንኛውም ተማሪው ብቁ-በሚሆንበት የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ውስጥ ለመካፈል ሲከለከል፣ እና
- ተማሪው ወይም የተማሪዎች ቡድን፤ የማንጓጠጥ (bullying) ወይም ትንኮሳ ተጠቂ ሲሆን - የወሲባዊ ትንኮሳ (Sexual harassment)ን ጨምሮ፣

ቅሬታዎች፤ በDCPS ፖሊሲ የተሰጠው የተለየ-የቅሬታ ሂደት ወይም የፍርድ-ቤት ተሰሚነት ሂደት (hearing process) የሌለው፤ በማንኛውም ሌላ በህግ የተሰጡ-መብቶች ጥሰቶች ላይ ፋይል ማድረግም ይችላሉ።

### A. የቅሬታ ሂደት

የDCPS፣ ሦስት ደረጃዎች ያሉት የቅሬት ሂደት አሉት: (1) ቅሬታን ሪፖርት ማድረግ፣ (2) ኤጀንሲን እውቅና መስጠት እና መርዳት፣ እና (3) ምርመራ (investigation)፣ ትንታኔ፣ እና መፍትሄ-መስጠት።

#### 1. ቅሬታን ሪፖርት ማድረግ

ቅሬታዎች፤ በሚከተሉት መንገዶች ሪፖርት መደረግ ይችላሉ:

- በቃል (Verbally): ሪፖርት አድራጊው፣ ወይም የተበሳጨው (aggrieved)፣ ከርዕሰ መምህሩ፣ የቅሬታ POCው፣ ማንኛውም የትምህርት ቤት ሠራተኛ፣ ወይም የDCPS ማዕከላዊ ቢሮ ሁሉን-አቀፍ አማራጭ መፍትሄ ሰጪ እና ፍትሃዊ-እኩልነት (Comprehensive Alternative Resolution and Equity (CARE) ቡድን[7] ጋር፤ በአካል ተገኝቶ (in person) ወይም በስልክ አማካኝነት ይነጋገራል።
- በጽሁፍ (Writing): ሪፖርት አድራጊው፣ ወይም የተበሳጨው (aggrieved)፣ ርዕሰ መምህሩን፣ የቅሬታ POCውን፣ ማንኛውም የትምህርት ቤት ሠራተኛን፣ ወይም የ'CARE' ቡድን አባልን በኢሜል በdcps.care@k12.dc.gov፣ አማካኝነት ወይም በስልክ በ(202) 442-5405፣ የታተመውን ቅጂ (hard-copy) እንዲላክ፣ ወይም በኦንላይ ቅጽ አማካኝነት በሚከተለው ማገናኛ ላይ የሚገኘውን፤ https://dcps.dc.gov/page/grievance-form በመጠቀም ማነጋገር ይቻላል።

የሰው-ልጅን መብቶች ክሶች ላይ ውንጀላን ያቀረቡ ሁሉም በቅሬታ-ላይ ፋይል የተደረጉ ሁሉ፤ ወደ 'CARE' ቡድኑ ሪፖርት መደረግ አለባቸው፤ ይህም ወይ በቀጥታ - ሪፖርት-በሚያደርገው-ሰው ወይም ደግሞ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ቅሬታውን በተቀበለው ሠራተኛ-አባል ሊሆን ይችላል።

#### 2. የኤጀንሲ (Agency) እውቅና-መስጠት እና እርዳታ

ሪፖርት በተደረገበት በአንድ (1) የትምህርት ቀን ውስጥ፣ በኢሜል አማካኝነት - ልዩ የጉዳይ መለያ፣ ክሶቹን፣ በምርመራ ሂደቱ ላይ የሚቀጥለውን እርምጃዎች፣ የተመደበውን-ሰው - እነዚህ መረጃዎች የያዘ ማስታወቂያ ለአካላቶቹ (parties) ይደርሳቸዋል

---

[5] 5-E DCMR § 2401.

[6] These grievance procedures will extend beyond schools or DCPS-sponsored activities when one or more DCPS student is involved, and the educational environment is impacted.

[7] Additional information about the CARE Team is available online at http://dcps.dc.gov/page/studentparentvisitor- grievance-process.

የመርማሪው ስም፣ እና የመፍትሄ ደብዳቤው (Letter of Resolution (LOR)፣ ይሰጣል ተብሎ የሚጠበቅበት ቀን። የኢሜል አድራሻ የማይገኝ ከሆነ፣ ማስታወቂያው በመደበኛ ደብዳቤ መላኪያ አማካኝነት ይሰጣል። ደብዳቤ የመላኪያ አድራሻ የማይገኝ ከሆነ፣ ማስታወቂያው በስልክ-አማካኝነት የሚሰጥ እና በኤሌክትሮኒክ በሰነድነት ይቀመጣል። ቅሬታው ማንነትን-ሳይጠቅስ (anonymously) ፋይል የተደረገ ከሆነ፣ ምንም-የኤጀንሲ ማስታወቂያ አይላክም።

አጋዥ-የሆኑ እርምጃዎች አስፈላጊ መሆናቸውን ለመወሰን፣ እያንዳንዱ ጉዳይ በግምገማ-ሂደት ውስጥ ያልፋሉ። አስፈላጊ-ነው ተብሎ ከተወሰነ፣ የ'CARE' ቡድን፣ መፈጸሙን-ለማረጋገጥ ከአካባቢው ትምህርት ቤቶች ጋር ይሠራሉ። አካላቶቹ (The parties)፣ የመፍትሄ ሂደቱን ለመዳሰስ ይረዳል-ብለው የመረጡትን አድቫይዘር ሊጠይቁ ወይም ሊሾሙ ይችላሉ። የሰብዓዊ መብቶች ወይም የአጠቃላይ ቅሬታው ባህሪ-ዓይነት፣ የልጅ-ጥቃት (Child Abuse) ወይም ቸል-መባል[8] ደርሶበታል ተብሎ የሚጠረጠረውን፤ የDCPS ሠራተኛው ሪፖርት እንዲያደርግ ያስፈልገው ይሆናል።

3. ምርመራ፣ ትንታኔ፣ እና መፍትሄ-መስጠት

ሪፖርት በተደረገበት በሁለት (2) የትምህርት ቀናቶች ውስጥ፣ የተመደበው መርማሪ፣ የምርመራ ሂደቱን ያስጀምራል። ምርመራ-ማድረግ፤ ማስረጃ የሚሆኑ-ነገሮችን መሰብሰብን ይጠይቃል። ማስረጃ (Evidence) የሚሆኑ የሚከተሉትን የሚያካትት፣ ነገር ግን በነዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ እንደ - ቅርሶች (artifacts)፣ የተፃፉ አባባሎች፣ የቃለ-መጠይቅ ማስታወሻ፣ የቪዲዮ ምስል፣ የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቶች፣ በማህበራዊ ሚድያ ላይ የተለጠፉ ነገሮች፣ የትምህርት ቤት መዝገቦች፣ እና የቁጥጥር መመሪያ (regulatory guidance) ናቸው። ሁሉም ክሶች፣ የምርመራ መረጃዎች፣ እና እንቅስቃሴ፤ በኤሌክትሮኒክ (electronically) ይቀመጣሉ።

የምርመራው-ሂደት በሚጠናቀቅ ጊዜ፣ ምርመራውን አድራጊው ሰው፣ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመተንተን እና በ'CARE' ቡድኑ በማስረጃ መደበኛነት ቅድመ-ሁኔታ ላይ መሠረት በማድረግ፣ ውሳኔውን ያስቀምጣል። መርማሪው፣ ከዚህ በመቀጠል የ'LOR' ረቂቁን በማዘጋጀት እና ከሚከተሉትን ውጤቶች ውስጥ ሊሆን የሚችለውን ያካትታል:

- **ተጠናቆ-ተሰናብቷል (Dismissed)**: ቅሬታው፤ ሙሉ-ምርመራ ሳይኖረው ተዘግቷል፣
- **ከግዛት-ስልጣኑ ውጪ (Outside of jurisdiction)**: ውንጀላው የCARE ቡድኑ ለማጣራት ከሚችልበት ውጪ በመሆኑ፤ አቤቱታን ጨምሮ - የተለየ የቅሬታ ሂደቶችን ወይም የፍርድ ቤት መሰማት ሂደቶችን (hearing processes) ጨምሮ፤ አቤቱታው በDCPS ውስጥ በሆነ-ወደ ሌላ ቡድን - እንደ ሚመለከተው ሁኔታ፤ ለምልከታ ሊመራው ይችላል፣
- **የተረጋገጠ (Substantiated)**: ውንጀላዎቹ፤ እውነተኛ ሆነው የተገኙ ወይም በማረጋገጫዎች ተደግፈው የተገኙ፤ እና 'DCPS'ም፣ በተገቢው የማረሚያ እርምጃዎች ውስጥ ይሳተፋል፣
- **ለማረጋገጥ ያልተቻለ (Unable to be substantiated)**: ውንጀላዎቹን ለማረጋገጥ ወይም ላለማረጋገጥ፤ በቂ-ያልሆነ የማረጋገጫ-እውነታዎ እንዳሉ ታይቷል፣
- **ያልተረጋገጠ (Unsubstantiated)**: ውንጀላዎቹ፣ በማረጋገጫ-እውነታዎች ያልተደገፉ ነበሩ፤ ወይም
- **ከመግለጽ የተቆጠበ (Withheld)**: የ'CARE' ቡድኑ፤ ምንም ግኝቶቹን በመግለጽ አይሰጥም።

ቅሬታዎቹ፤ ቅድመ-ምርመራው ተካሂዶ ከተጠናቀቀ በኋላ ሊዘጋም ይችላል። ጊዜው እንዲራዘም አካላቶቹ (parties) ካልተስማሙ በስተቀረ፤ ሪፖርቱ ካገኙበት ሠላሳ (30) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ አካላቶቹ (Parties) 'LOR'ን ያገኛሉ።

ቅሬታዎችን ምላሽ-በመስጠጥ እና 'LOR'ን በመስጠት ላይ፤ የCARE ቡድኑ፣ አጠቃላይ የተበሳጩትን አካላቶች (parties) እና ማንኛውንም ስልታዊ ውድቀትን ለማረም ይጠይቃል። ይህ ወደ ፖሊሲ ለውጦች፣ የአገልግሎት ድንጋጌ፣ እና/ወይም ከመልስ-ሰጪው ጋር በሚኖር የስነምግባር እርምጃን ሊመራ ይችላል። የስነምግባር እርምጃ፣ ከDCPS የተማሪ የስነምግባር ፖሊሲዎች[9]ጋር በተያያዘ የሚከናወን ይሆናል።

---

[8] All DCPS staff are mandatory reporters required to report suspected child abuse or neglect to DC Child and Family Services and the Metropolitan Police Department. For additional information, see http://bit.ly/DCPSMandatedReporterFAQ.

[9] *Available at* https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies.

### B. የአንቀጽ 9 (Title IX) የምርመራ ሂደቶች

በአንቀጽ 9 (Title IX) የቅሬታ ክስ-ጥሰቶች በሚቀርቡ ጊዜ፣ መደበኛ የጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክ ቅሬታው፣ በተበሳጨው-ሰው ወይም በወላጃቸው/አሳዳጊያቸው[10] ፋይል መደረግ አለበት። የወሲባዊ ትንኮሳ (Sexual harassment) ክስ ላይ የቀረበ ቅሬታ፣ በመልስ-ሰጪ(ዎች) እና DCPS ምርመራዎችን እንዲያካሂድ መጠየቅ አለባቸው። ህጋዊ የሆነ አንቀጽ 9 (Title IX) ቅሬታዎች፤ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላትም ያስፈልጋቸዋል:

- የአንቀጽ 9 (Title IX) ቅሬታን ፋይል ያደረገ ተማሪ፣ ወይም እነርሱን ወክሎ ቅሬታው ፋይል የተደረገላቸው፤ በDCPS ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ መካፈል ወይም ለመካፈል ሙከራ ማድረግ አለበት።
- DCPS፣ በምላሽ-ሰጪው ላይ እና የወሲባዊ ትንኮሳው (Sexual harassment) በተካሄደበት - አባባሎች (context) ላይ ከፍተኛ-የሆነ ቁጥጥር ማድረግ አለበት።
- እንቅስቃሴው፤ (1) በአሜሪካ አገር (United States) ውስጥ እና በDCPS ንብረት-በሆነ ቦታ ውስጥ፣ (2) ከDCPS ንብረት-ውጪ በሆነ - በDCPS-ስፖንሰር በተደረገ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት፣ ወይም (3) በኦንላይን ክፍለ-ጊዜ በሚከናወንበት ጊዜ፤ የተከሰተ መሆን አለበት።

ቅሬታው፣ እንደ አንቀጽ 9 (Title IX) ቅሬታ ሆኖ ለመወሰድ መስፈርቱን የሚያሟላ ካልሆነ፣ ወይም ቅሬታ-አሰሚው ህጋዊ የአንቀጽ 9 (Title IX) ቅሬታን ፋይል ለማድረግ ካልፈለገ፤ ወይ ይዘጋል ወይ-ደግሞ በሌላ ምድብ-ስር ፋይል ይደረጋል። የአንቀጽ 9 (Title IX) ቅሬታ፤ ተጠናቅቆ እንዲዘጋ (dismissed) ሊያደርገው የሚችለው፤ ቅሬታ-አሰሚው ቅሬታውን እንደተወውና እንዲነሣ (withdrawn) በጽሁፍ ከጠየቀ ነው። ቅሬታ-አሰሚው ህጋዊ የአንቀጽ 9 (Title IX) ቅሬታን ፋይል ማድረግን በማይቀበልበት-ጊዜም ቢሆን፤ አስፈላጊ በሆኑ ጊዜ፣ ደጋፊ የሆኑ እርምጃዎች (Supportive measures) የሚሰጡ ይሆናል።

### C. ይግባኞች እና የአቤቱታ ሂደት (Appellate Procedure)

ይግባኝ፣ ከሁለቱ በአንደኛ አካል (party) መጠየቅ ይችላል። ይግባኝ የሚከናወንበት ብቸኛ የሆኑ ምክንያቶች፤ አዲስ መረጃ ካለ፣ በውጤቱ ላይ ተጽዕኖ ያደረገ የስርዓት ጥሰት እንደነበረ ማስረጃ ካለ፣ ወይም በውጤቱ ላይ ተጽዕኖ ያደረገ በአግባብነት ያልተሰራ-የተጋጩ ነገሮች (conflict of interest) መኖራቸው ማስረጃ ካለ ብቻ ነው። የይግባኝ ጥያቄ፣ በጽሁፍ - LORን በተቀበሉ በሰላሳ (30) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ መግባት አለበት። ይግባኙ፤ በይግባኝ ምልከታ ፓነል (Appeal Review Panel)፣ ፊት ቀርቦ፣ ተገቢ እና ተመጣጣኝ-የሆነ መፍትሄ መሰጠቱን ለማረጋገጥ፣ ይቀርባል። ፓነሉ (The panel)፣ በአመራር ስልጣን ላይ ያሉ፤ በቻንስለሩ ወይም በተወካዩ የተመረጡ - ሦስት (3) ሰዎችን ያካተተ መሆን አለበት። የይግባኝ ምልከታ ፓነል (Appeal Review Panel)፣ ሁሉንም መረጃዎች ይመለከት እና፤ ለDCPS የሃቀኝነት ሹሙ ዋና የሆነውን (Chief Integrity Officer) ወይም ለቻንስለሩ ተወካይ፣ ለመፍትሄው ያቀረበውን ግኝቶች እና የሚያቀርበውን ሃሳቦች በጽሁፍ ያቀርባል። ግኝቶቹ እና የቀረቡት-ሃሳቦች፤ ፓነሉ (the panel) በተቀበለበት፣ በሃያ (20) ቀናት ውስጥ የሚሰጥ ይሆናል። የሃቀኝነት ሹሙ ዋና የሆነውን (Chief Integrity Officer) ወይም ሌላ የተወከለው ሰው፤ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔውን ለሁሉም አካላቶች (all parties)፤ በጽሁፍ - የፓነል ሃሳብ መስጫዎቹን በተቀበሉበት በሃያ (20) የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ይሰጣሉ።

### D. ሚስጢራዊነት (Confidentiality)፣ ስምምነት-መስጫ (Consent)፣ እና የበቀል-እርምጃ (Retaliation)

DCPS፣ በቅሬታ መፍታት ሂደቱ ወቅት፣ ሚስጢራዊነትን በከፍተኛ በሚችለው ደረጃ በመጠበቅ ይሠራል።

የተበሳጨው-ሰው/ምላሽ-ሰጪው/ምስክሩ፤ እድሜያቸው ከአስራ ስምንት (18) ዓመት በታች ከሆኑ፤ በምርመራው ውስጥ ለመካፈል፣ ከወላጆች ስምምነት-መስጫ (Consent) ማግኘት ያስፈልጋል። ቅሬታው ማንነትን-ሳይገልጽ (anonymously) ፋይል የተደረገ ከሆነ ወይም ሪፖርት-አድራጊው/የተበሳጨው ሰው፣ በምርመራ ሂደቱ ውስጥ ላለመግባት ከፈለጉ፤ ሚስጢራዊነታቸውን ወይም ያለመካተት[11] ጥያቄያቸውን በማክበር፣ ምርመራውን ለማድረግ እና ለሪፖርቱ/የቅሬታው ምላሽ-ለመስጠት DCPS ሁሉንም ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳል።

[10] All complaints alleging potential Title IX violation will be initially investigated under Title IX procedures regardless of whether the complaint specifically names or cites to the statute.

[11] The outcome may be hindered without full participation of all parties.

ከቅሬታው ፋይል መደረግ ጋር ግንኙነት ባለው ማንኛውም አካል ላይ የሚደረግ የበቀል-እርምጃ (Retaliation)ን፣ በጥብቅ ይከለክላል። የትምህርት ቤት ሹሞች፣ የበቀል-እርምጃውን (retaliation) ለመከላከል፣ ሁሉንም የሚገኙ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው። ይህ የበቀል-እርምጃ (retaliation) በሚከሰት ጊዜ፣ DCPS ጠንካራ የምላሽ እርምጃዎችን ይወስዳል።

### E. ከDCPS ውጪ-የሚገኙ ማዳኛ-መድኀኒቶች (Remedies)

አንድ-ሰው፣ ስጋቶቹ በDCPS እንዲፈታለት ካልፈለገ፤ ያለውን አቤቱታ በሚከተሉት በማንኛውም የውጪ-ድርጅቶች አማካኝነት አቤቱታን ፋይል ማድረግ ይችላል:

1. የአሜሪካ የትምህርት መምሪያ (U.S. Department of Education)፣ የሰው-ልጅ መብቶች ቢሮ (Office for Civil Rights)

ቅሬታ አሰሚው፣ አቤቱታውን በቀጥታ ከአሜሪካ የትምህርት መምሪያ፣ የሰው-ልጅ መብቶች ቢሮ (U.S. Department of Education, Office of Civil Rights (OCR)፤ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ያሉትን ማንኛውም ሂደቶችን ሳያጠናቅቅ ወይም፤ ካይከተልና፣ ሳይጠቀም፤ ፋይል ማድረግ ይችላል። ከ'OCR' አቤቱታን ፋይል የሚያደርግ ከሆነ፤ ደረሰ-የተባለው አድልዎ ወይም ትንኮሳ ከተከሰተ-በኋላ፣ የ180 ቀናቶች ጊዜ ሳያልፍ በጽሁፍ ፋይል መደረግ አለበት። ተጨማሪ መረጃዎች፣ በhttp://www.ed.gov/ocr/complaintprocess.html ላይ ይገኛል።

2. የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (District of Columbia Office of Human Rights)

ቅሬታ አሰሚው፣ አቤቱታውን በቀጥታ ከኮሎምብያ ዲስትሪክት የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (District of Columbia Office of Human Rights)፣ የDCPS የቅሬታ ሂደቶችን ሳይከተል ወይም ሳይጠቀም፤ ፋይል ማድረግ ይችላል። አቤቱታው፤ ደረሰ-የተባለው አድልዎ ወይም ትንኮሳ በተከሰተ በአንድ (1) ዓመት ውስጥ ፋይል መደረግ አለበት። ተጨማሪ መረጃዎች፣ በhttp://www.ohr.dc.gov. ላይ ይገኛል።

## V. ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚፈለጉ መስፈርቶች

ሁሉም የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኞች፤ በዚህ በተቀረጸው ፖሊሲ መስፈርቶች መገዛት ያስፈልጋቸዋል። ስለ እዚህ ፖሊሲ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ወደ ስጋቶችን በተመለከተ፣ ለ'CARE team' በdcps.care@k12.dc.gov በቀጥታ መጠየቅ ይችላሉ። ይህ ፖሊሲ የሚያከትላቸው-ነገሮች፤ በ'CARE' ቡድን የሚጠናከሩ ይሆናል።

DCPS እያንዳንዱን ተማሪ፤ በፍህታዊነት፣ የላቀ-በላጭነት፣ ግልጽነት፣ እና ተጠያቂነት ባለው-ሁኔታ ለማገልገል ቁርጠኝነቱን የሚያሳይ እና ለተማሪዎች የአድልዎ እና ከጥቃት ነፃ የሆነ አካባቢን መፍጠር ነው። ስለ ማንኛውም ስጋቶች ወይም ጥሰቶች ናቸው ተብሎ በዚህ መመሪያ ውስጥ የታመነባቸው ነገሮችን ላይ፣ የሃቀኝነት ሹሙ ዋና የሆነው (Chief Integrity Officer)ን ለማነጋገር፤ የኦንላይን የመምራት (Referral) ቅጽን[12] በመሙላት ወይም ወደ dcps.cio@k12.dc.gov ኢሜል መላክ።

[12] *Available at* https://dcforms.dc.gov/webform/online-referral-form.